# የብልጽግና ፓርቲ ሲቶች ሊግ ፕሮግራም

ግንቦት 2012

አዲስ አበባ

**መግቢያ**

የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ህብረተሰባዊ ለወጥን የማፋጠን፤ የወቅቱን መድረክ ተልዕኮ ተገንዝቦ በብቃት የመፈፀም፤ ሁሉንም ሴቶች ለጋራ አላማ የማሰለፍ፤ የትግል መድረክ ሆኖ የማገልገል፤ እና ከትግሉ የሚገኙትን ጥቅሞች የማጣጣም ቁልፍ እና ወሳኝ ተልዕኮ አንግቦ የብልፅግና ፓርቲን የፖለቲካ እንቅስቃሴ በሴቶች ዉስጥ ለማስረጽ የተደራጀ የፖለቲካ አደረጃጀት ነው፡፡ ሀገራችን አሁን ከደረሰችበት የኢኮኖሚ የማህበራዊ እና የፖለቲካ እድገት አንፃር የተገኙ ድሎችን አስጠብቆ ለማስፋት ስህተቶችን ለማረም ወቅታዊ ሁኔታውን እና የብልፅግና ፓርቲ ሁለተናዊ ሪፎርሙን በመገንዘብ የሴቶችን ሁለተናዊ ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በየደረጃው ያሉ የሊጉ አመራር እና አባለት ወሳኝ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ፓርቲያችን ብልጽግና በፕሮግራሙ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የነበረውን ጠንካራ መሠረት በማስጠበቅ እና ውስንነቶችን በማረም ሁለንተናዊ የብልፅግና ምዕራፍ የመክፈት፤ በተለያዩ ቡድኖች፣ መደቦች፣ ማንነቶች. ወዘተ የሚስተዋሉ ዋልታ ረገጥ አስተሳሰቦችን ሚዛን ጠብቀው እንዲሄዱ ማድረግ፤ ቋሚ መርሖዎችን ማዕከል በማድረግ ጉዞን የመፈተሽና በጥናት ላይ የተመሠረተ የተግባራዊነት ዕሳቤን ይዞ በኢህአዴግ የተለዩ ችግሮችን በሪፎርም የማስተካከል ተግባር እየተፈፀመ በመሆኑ ሊጉም ከነበሩበት የአሰራር እና የአመራር እንዲሁም የተልዕኮ ችግር ለመላቀቅ ሪፎርሙን በመቀበል እራሱን እንደገና ማደራጀት የግድ ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም ሊጉ በቅርፅም በይዘትም መቀየር አለበት ፤ እንዲሁም ነባር አባሎቹንና አዳዲስ የብልፅግና ፓርቲ ሴት አባላትን በማደራጀት የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ሁኖ በመቋቋም ከፓርቲው የተቀዳ የመታገያ ፕሮግራም ይዞ መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡

በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ዛሬም ዋነኛ ጠላቶቻችን ድህነት እና ኋላቀርነት እንደ መሆናቸው መጠን በመደመር መንገድ ወደ ብልጽግና በሚደረገዉ ጉዞ ሴቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆን ስለሚገባቸዉ ፓርቲያችን በነደፋቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና በሚነድፋችው ስልቶች የአገራችንን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን የመፍታት ሂደትና በልማትና ዴሞክራሲ ተግባር ሴቶችን በተደራጀ አኳኋን ማሳተፍ ዘላቂ ዋስትና መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

በፆታ መካከል በነበረው የተዛባ አመለካከት ሳቢያ የተፈጠረውን የሥርዓተ - ፆታ ክፍተትና በሴቶች ላይ የተመዘገበውን አሉታዊ የታሪክ ቅርስ ማረም እንዲቻል በሕገ - መንግስቱ አንቀፅ 35 ላይ የሴቶች ጉዳይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ተቀምጧል፡፡ አድሎአዊ ሕጎች ተሻሽለዋል ሕገ መንግስቱን መሠረት አድርገው የወጡ ሌሎች ሕጎች ደንቦች ፖሊሲዎችም ሥርዓተ - ፆታን ባካተተ መልኩ እንዲቀረጽ ተደርጓል፡፡ ከፌደራል እስከ ቀበሌ ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ መንግስታዊ እና ህዝባዊ አደረጃጀቶችን በመዘርጋት አበረታች ውጤቶች ታይተዋል፡፡

እስካሁን ድረስ በተካሄዱት ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ርብርቦች ሴቶችን ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደረጉ ጥረቶች ቢኖሩም ከሴቶች ተጨባጭ ችግሮችና ፍላጎቶች ጋር የሚመጣጠኑ ባለመሆናቸው በተሳትፏቸው መጠን ተጠቃሚ እንዲሆኑ መታገል ያስፈልጋል፡፡ በሁሉም መስክ እያስመዘገብን ያለነው እድገት እንደ ተጠበቀ ሁኖ አሁንም የወንድ የበላይነት አመለካከት በመኖሩ በሴቷ ብቃት እና ችሎታ አለማመን እና ሴቶችም እችላለዉ ብለዉ አምነው ከመቀበል ይልቅ በወንዶቹ አመለካከት የመዋጥ ዝንባሌዎችን በህብርና በአንድነት በመሆን መታገልና ከመጪው ትውልድ አስተሳሰብም ጭምር እንድቀረፍ ሰፊ ስራ መስራት ይጠይቃል፡፡

በአገራችን ድህነትንና ኋላቀርነትን ድል አድርጎ ብልጽግና፣ ፍትህና ዴሞክራሲን የዳበረ ደረጃ ላይ ለማድረስ የሚካሄደው ትግል ሊሳካ የሚችለው ትግሉ በመደመር እሳቤ በመግባባት ዴሞክራሲ በፓርቲያችን ጥላ ስር ሊጋችን ሲመራ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ በመሆኑም የብሔር ማንነትን እና የሀገራዊ አንድነትን ሚዛን የጠበቀ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት ውስጥ የሊጉ አባላትና አመራሮች እንዲሁም መላው የሀገራችን ሴቶች የጠራ ህዝባዊ አመለካከት ኖሯቸው ተገቢውን እንዲወጡ በመቅረጽ ሀገራዊ መግባባት በሚያመጡ፣ የሕዝቦችን ግንኙነት በሚያሳልጡ ፖለቲካዊ እርምጃዎች ትኩረት አድርጎ በመንቀሳቀስ ተቋማዊና ሕዝባዊ ባህል ላይ የቆመ የዴሞክራሲ ሥርዓት በመገንባት ዘላቂና አዎንታዊ ሰላምን ለማረጋገጥ የሚደረገውን አገራዊ ጥረት መደገፍና የሚጠበቅብንን መወጣት ይኖርብናል፡፡

ኢህአዴግ በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ሂደት ሴቶችን በሊግ አደራጅቶ በማንቀሳቀስ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ ለማድረግ ቢንቀሳቀስም መላዋን የአገሪቱን ሴቶች በእኩል ባለማንቀሳቀስ የተወሰኑትን አካባቢዎች ባገለለ አካሄድ አመራር ሲሰጥ የነበረውን በማስተካከል በመደመር እሳቤ አባልና አጋር ሊጎች ዉህደት በመፍጠር ለመላው የሀገራችን ሴቶች ተደራሽ መሆን አስፈላጊ መሆኑን አምነናል፡፡ እንዲሁም ለአገራችን እድገት ጸር የሆኑትን እና የሴቶችን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት የሚገቱ አስተሳሰቦችን በመታገል አገራችን የጀመረችውን ሪፎርም በማቀላጠፍ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እና የማህበራዊ እድገት በማፋጠን የሴቶችን ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት ማረጋገጥ እንደሚቻልም እናምናለን፡፡

ስለሆነም በጉባኤያችን ውሳኔ መሰረት ሊጉ እድሎቹን አሟጦ የመጠቀም፣ ተግዳሮቶቹን በቁርጠኝነት የመፍታት፣ ብልፅግና ፓርቲ ባለቤትነት እና በለውጡ ላይ የአመለካከትና የተግባር አንድነት በማረጋገጥ የለውጥ ሂደቱን ሴቶች በብቃት ለመምራት የሚያስችላቸወን ፖለቲካዊ ጥንካሬ እንዲኖራቸው ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ በአጠቃላይ በመደመር አስተሳሰብና ሁለንተናዊ የሴቶችን ብልፅግና በማረጋገጥ የበለፀገች ኢትዮጵያን ለመገንባት የእያንዳዳችን ርብርብ የሚጠይቅ መሆኑን በመረዳት የበኩላችንን ሚና ለመጫወት በከፍተኛ ቁርጠኝነት ተሰባሰበን ይበልጥ በተጠናከረ መልኩ ለመታገል በማስፈለጉ የብልፅግና ፓርቲ ውህደትን በመከተል በ4ኛው የሊጋችን ጉባኤ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የፓርቲዉን ተልዕኮ እና ውሳኔ ለማስፈፀም እና የሴቶችን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ የየብሄራዊ ድርጅቱ አባል ሊጎችና አጋር

ሊጎች እዲዋሀዱ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በአገራችን በሁሉም ክልል በሚገኙና  የብልፅግና ፓርቲን ከመሰረቱት ፓርቲዎች ሴቶች ሊጎች ጋር  በጋራ የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ በማደራጀት ይህንን ከፓርቲው የተቀዳ ፕሮግራም አዘጋጅተዋል ፡፡

በመሆኑም በብልጽግና ፓርቲ ፕሮግራም የተዘረዘሩትን ግቦች በማሳካት ከድህነትና ኋላቀርነት የተላቀቀች፣ ሕብረ ብሔራዊ አንድነቷን ያስጠበቀች እና የበለፀገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር የተያዘውን አላማ በመቀበል ከብልፅግና ፓርቲ ጥላ ስር በመሰባሰብ ቀጥለዉ ለተዘረዘሩት የሊጉ መለያ እሴቶችና አላማዎች የሚታገል ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት በቁርጠኝነት እና ተነሳሽነት በበለጠ ሓላፊነት እና አላማው ከትዉልድ ወደ ትዉልድ የሚተላለፍበትን አቅጣጫ በመከተል ሊጉ በቀጣይ የተዘረዘሩትን እና በሕገ ደንባችን የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ለመፈፀም ሊጉ የሚታገልላቸዉን ሴቶች በማሰባሰብና በማደራጀት በአገራችን የተጀመረዉን የለዉጥ ጉዞ የፓርቲያችንን ሪፎርም ለማስቀጠል የተዘጋጀ እና ሁሉም የሊጉ አባላት እና አመራሮች ሊፈፅሙት እና ሊተገብሩት የሚገባቸዉ ፕሮግራም ይሆናል፡፡

## የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አላማ እና መለያ እሴቶች

### ጥቅል አላማ

የበለፀገች እትጵያን እዉን በማድረግ የሴቶቻችን ሁለንተናዊ ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፡፡ ብልፅግና የሚገለፀዉ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ እና በማህበራዊ ገፅታዎች  ይሆናል፡፡ ሊጋችን የኢኮኖሚ ብልፅግና የሴቶች መሰረታዊ ፍላጎቶች በተገቢዉ እና በዘላቂነት በመሟላት ፈጣን እና ሁለንተናዊ  ዕድገትን አስመዝግበዉ ተወዳዳሪ የሆኑ ሴቶችን ማፍራት እና ማበራከት ስንችል  እና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ተረጋገጦ ሴቶች ከወንዶች እኩል ሀብት የማፍራት የማስተዳደር እና የማካበት መብታቸዉ መረጋገጥን ያካትታል ፡፡ የፖለቲካ ብልፅግና ሲባል ሴቶች ህገ መንግስታዊ እና ሰብአዊ መብቶቻቸዉ ተረጋግጦ እና ተከብሮላቸዉ በየደረጃው በሁሉም የዉሳኔ ሰጭነት ቦታዎች እኩል የመሳተፍ መብታቸዉ ሲረጋገጥላቸዉ ማየት እና ህብረ ብሔራዊ አንድነቷ የተረጋገጠ ፌዴራላዊ ዴሞክረሲያዊት ኢትዮጵያ በፅኑ መሰረት ላይ ቁማ የሴቶች እኩልነት የተረጋገጠበት አገር ስትሆን ማየት ይሆናል፡፡ ማህበራዊ ብልፅግና ሲባልም ሴቶች ለዘመናት ሥር ሰዶ  የቆየውን በፆታ ላይ የተመሠረተ ባህላዊና ልማዳዊ አድሎአዊ አስተሳሰብ  ደረጃ  ማጥፋትና ካለዉ አገራዊ ልማዶች እና ወጎች በመነሳት ያሉን መልካም እሴቶች እና ባህሎች በማጎልበት በስነ ምግባር የታነፀች ሴትን በመፍጠር ለትዉልዱ አርአያ የሚሆኑ ጤናማ አመለካከት እና አስተሳሰብ የተጎናፀፉ ትዉልድና ቤተሰብ በመፍጠር  ከአስከፊ ማህበራዊ ችግሮች ባህላችን ካልሆኑና ትዉልድን ሕዝብን እና አገርን ከሚጎዱ ልማዶች እና ዎጎች የፀዱ እሴቶች በመገንባት በሕዝቦች መካከል አዎንታዊ ሰላም ተፈጥሮ ሁለንተናዊ ብልፅግና ማረጋገጥ፡፡

**መለያ እሴቶች**

ለብልፅግና ዓላማችን ቅድሚያ በመስጠት የምንታገልለት እና መዳረሻ መንገዳችን የሚሆኑን አገራዊ እሴቶቻችን ይሆናሉ ። ስለሆነም ማንኛዉም ችግር እና ፈተናዎች ቢገጥሙን እንኳን ወደ ብልፅግና ከምናደርገዉ ጉዞ /መንገድ የሚገቱንን ከታጋይ ወንድሞቻችን ጎን እኩል በመሰለፍ ባይሳኩ ይበልጡንም ሴቶችን ብሎም ማህበረሰቡን የሚጎዱ ከመሆናቸዉ አንፃር በፅናት እና ቁርጠኝነት የምንታገላቸዉ እሴቶቻችን ይሆናሉ። እነርሱም ፡-

- **ህብረ-ብሔራዊ አንድነት፡-** ብዝኃነታችንን እንደ ፀጋ የምትመለከት እና ለሁሉም ብዝኃነቶች እዉቅና የምትሰጥ በመኻላቸዉ የታሪክ ትስስር ተመሳሳይነት የጋራ ጥቅም እና ተስፋ በመነሳት ጠንካራ ህብረት እና ትስስር እንዲኖረን መታገል። ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን ለማረጋገጥ የኢትዮጵያ ሴቶች በህብረት ሁነን እንበለጽጋለን፤ በልፅገንም በህብረት ለመኖር እና የትዉልድ የቤተሰብ እና የአገር ክብርና ኩራት እንሆናለን።
- **የዜጎች ክብር፡-** ኢትዮጵያዊያን ሴቶች በሐይማኖት በብሔር በሀብት እና በድህነታቸዉ ሳይከፋፈሉ የሁሉም ሴቶች መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸዉ በእኩል አይን ሲታይ እና ፍትህ አግኝታ በዋና ዋና የአገሪቱ ገዳዮች ላይ ዉሳኔ መስጠት ስትችል ማየት። ሴት በሴትነቷ እና በዜግነቷ የሚገባት ክብር እንዲኖራት በመስራት በግለሰብ በማህበረሰብ እና በአገር ደረጃ የሚታዩ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች በየትኛዉም ቦታ በአገራቸዉ በማህበረሰባቸዉ እና በሴትነታቸዉ እንዲኮሩ ማድረግ።
- **ነፃነት፡-** ሴቶች የራሳቸውን የሕይወት ራዕይ የመምረጥና በመረጡት መንገድም የመኖር መብታቸው እንዲረጋገጥላቸው፣ መጻፍ፣ ማንበብ፣ እና የፈለጉትን ሐይማኖት የመከተል መብቶቻቸዉን ማረጋገጥ።
- **እኩል ተሳታፊነትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት፡-** ሴቶች በኢኮኖሚ፣በማኅበራዊና በፖለቲካ መስክ ከሚገኙበት ኋላቀርነትና የበታችነት ተላቀው በሁሉም መስክ እንዲሳተፉ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብታቸው ማክበር ሁኔታቸውን ማሻሻል፣ማሳደግና ማጉልበት፣ እንዲሁምሴቶችን ሁኔታ ለማሻሻል እንቅፋት የሚሆኑ እንደ ሕግ፣ ባህል ወግና ልማድ ያሉ ጉዳዮች እንዲሁም የነዚህ ነፀብራቅ የሆነው አመለካከት ተወግዶና ተሻሽሎ በውሳኔ ሰጭነት ተግባር ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ለዚህም ሁኔታዎችን ማመቻቸት።

## የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ የፖለቲካ መርሃ ግብር

### የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ፖለቲካ ፕሮግራምና ዓላማ፡-

የፓርቲያችን የብልጽግና አላማ ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ዘላቂ ሀገረ መንግሥት መገንባትን ለማሳካት የፓርቲዉ አባል የሆኑትን ሴቶች አደራጅቶ የትግል መድረክ ሁኖ በማገልገል ሴቶች ሚና በጠንካራና

ቅቡልነት ያለዉ የአገረ መንግስት ግንባታ ዉሰጥ ጎልቶ በመታየት በየደረጃው እኩል ፖለቲካዊ ተሣትፎና የውሣኔ ሰጪነት ሥልጣን እንዲኖራቸው በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና በህገ-መንግስቱ ዙሪያ ዘላቂ ተሣታፊና ተጠቃሚ ማድረግ ይሆናል፡፡

- ሴቶች የብሔር ማንነትን እና የሀገራዊ አንድነትን ሚዛን በማስጠበቅ በሀገረ መንግሥት ግንባታዉ ማይተካ ሚና ይኖራቸዋል፣
- የሀገረ መንግስት ግንባታ ጅምራችን ጠንካራና የማይናወጥ ተቋማዊ መሰረት ያለው ለማድረግ ሁለንተናዊ ተሳትፎ ከሴቶች ይጠበቃል፣
- የፓርቲውን የዲሞክራሲ ባህል ሴቶች አደረጃጀት እና በተቋማዊ ባህል ላይ ለመገንባት፣
- የብልፅግና ፓርቲ የአንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የመፍጠር አላማ በማሳካት የሴቶች ሚና እንዲጎላ፣
- ሴቶችን ሀገራዊ መግባባት በሚያመጡ፣ የሕዝቦችን ግንኙነት በሚያሳልጡ እና የዕርቅ መንፈስን በሚያጎለብቱ ፖለቲካዊ እርምጃዎች ላይ ትኩረት በመስጠት ለማንቀሳቀስ፣

## የፖለቲካ ፕሮግራም ግቦች

- በሀገራችን በሚደረገው የፖለቲካ እንቅስቃሴና መልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ ለማስፈን በሚደረገው ትግል ሴቶች ንቁና የተደራጀ ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማድረግ ከውጤቱም ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ፣
- ጠንካራና ቅቡል ሀገረ መንግስት በጽኑ መሠረት ላይ ለመገንባት የሚያስችል ሀገራዊ መግባት የተጎናፀፈች ሴት ዜጋ መፍጠር፣
- በተቋማዊና ሕዝባዊ ባህል ላይ የቆመ የመግባባት ዴሞክራሲ ሥርዓትን በመገንባት የሴቶችን ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት ማጎልበት፣
- ዘላቂ አዎንታዊ ሰላምን በማረጋገጥ የሴቶች ጥቃት፣ ጉዳት
- እና አድሎ በመከላከል የሴቶችን እኩልነትንና በሰላም ወጥቶ መግባት እንዲሁም በሰላማዊ ስፍራ ተረጋግቶ የመኖር ዋስትናቸዉን ማረጋገጥ
- በሕገ-መንግሥቱ በቤተሰብና በወንጀል ሕግ የተከበሩ የሴቶች መብቶች ተግባራዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
- ሕብረተሰቡ በሴቶች ላይ እንዲሁም ሴቶች በራሳቸው ላይ ያላቸው የዝቅተኛና የበታችነት አመለካከት ተወግዶ በእኩልነት ላይ የተመሠረተጤናማ ግንዛቤ መፍጠር፣ ሁኔታዎችንም ማመቻቸትና ማዳበር፣

- ➢ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሴቶችን ጥቅም የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ሕጐችና ደንቦች፣ ኘሮግራሞች፣ ዕቅዶችና ኘሮጀክቶች በሚወጠኑበት፣ በሚዘጋጁበትና ሥራ ላይ በሚውሉበት ጊዜ ሴቶች የተሳተፉባቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ ተግባራዊነታቸውንም መከታተል፣

**የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ የኢኮኖሚ ፕሮግራምና ዓላማ፡-**

- ፓርቲያችን በያዘዉ ልማትና ፍትሀዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ አካታች የኢኮኖሚ ሥርዓት ግንባታ ዉስጥ የሴቶችን ሚና በሁሉም መንገድ በማረጋገጥ በሀገራችን በሚካሄደው ልማት ሴቶች ንቁ ተሣታፊና ከሚገኘው ኢኮኖሚ እድገት እኩል ተጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይሆናል፡፡

  - ➢ የሴቶች የኢኮኖሚ ሁኔታ ሲባል ሴቶች የባለቤትነት መብት ኖሮአቸው በጥሬ ገንዘብና በቋሚ ንብረት የሚያገኙበትን ሀብት የሚጠቀሙበትንና የሚያስተዳድሩበትን ሁኔታ የሚመለከት በመሆኑ በየትኛውም ቦታ በሴቶች የሚደረጉ ኢኮኖሚያው እንቅስቃሴዎች በሰላምና በነፃነት እንዲሆኑ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማረጋገጥ፣
  - ➢ ሀገራዊ ትስስርን ለሚያረጋግጡ የመሠረተ ልማት ግንባታ ሂደት የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣
  - ➢ የመንግስት በኢኮኖሚው ሥርዓት ውስጥ ያለው ተሳትፎ የገበያ መርሕን በመከተል በስትራቴጂካዊ በሆነ ሁኔታ ሀብትን ለመፍጠር በሚደረገዉ አካሄድ ሴቶችን ማነሳሳት፣
  - ➢ በተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ አስተዳደር ማዕቀፍ ውስጥ ሴቶች በግልም ሆነ በመደራጀት ከሌሎች የኢኮኖሚ ተዋናዮች ጋር ያላቸዉን ተሳትፎ በማጎልበት ምርታማነትን በላቀ ደረጃና ቀጣይነት ባለው መልኩ ማሳደግ፣

## የኢኮኖሚ ግቦች

- ➢ ሴቶች በግብርና በኢንዱስትሪና በሌሎችም በብዝኃ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዘርፎች የተዋቀሩና ዘላቂ ዕድገት ያላቸዉ እንዲሆኑ መስራት፤
- ➢ ሴቶች ከግብርና ዘርፉ በግብዓትና ቴክኖሎጂ አቅርቦት እንዲሁም አመራረትና የገበያ ትሥሥር መሠረት የመጠቀምና የመሳተፍ አቅማቸዉ ጎልብቶ ግብርናን የማዘመን ስራ መስራት፤

- የቤተሰብ ገቢ ማሳደግ እንዲቻል አስፈላጊው ግብዓቶችን በማቅረብና ተገቢ ሥልጠና በመስጠት ሴቶች በአትክልት፤ ፍራፍሬ እና በጓሮ አትክልት ልማት ሥራዎች ማሳተፍ
- ሴቶች በጥምር ግብርና ሥራዎች ላይ ውጤታማ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ሥልጠናና የሙያ ድጋፍ መስጠት፤
- በተለይ በተለይ በእርጥበት አጠር አካባቢዎችም ሆነ ሌሎች አካባቢዎች ሴቶች ውሃን ማእከል ያደረገ ተግባር በማከናወን ረገድ ሊጉ የግንባር ቀደምነት ሚናውን እንዲጫወት ማድረግ፤
- የመሬት ጥበት ባለባቸው አካባቢዎች እርሻን ማእከል ያላደረገ የልማት እንቅስቃሴና አነስተኛ እንስሳትን፣ የንብ ማነብ ስራን ማእከል ያደረገ የእንስሳት ሀብት ልማት ስራዎች እንደ የአግሮኢኮሎጂው እንዲሳተፉ በግንባር ቀደምነት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ፤
- በገጠር በሚካሄዱ የሸቀጣሸቀጥ ፣ ምግብና ባልትና የመሳሰሉ አነስተኛ የንግድ ሥራዎች ላይ የሚኖራቸውን ስምሪት ማጠናከር፣ እንዲሁም በአነስተኛ አግሮ ፕሮሰሰንግ ሥራዎች እንዲሰማሩ ማድረግ፤
- የአርብቶ አደር ሴቶችንና ከፊል አርብቶ አደር የሆኑትን ሴቶች አካባቢያዊ የተፈጥሮ ጸጋዎችን እና የኑሮ ዘዬ መሰረት ያደረገ ዘመናዊ ሴት አርብቶ አደር ልማትን በማመካሄድ ሴቶችን በእንስሳት እርባታ በማደለብ ፣ በወተትና በወተት ተዋጽኦ ምርት እና ንብ በማንባት፣ የዶሮ እርባታ ሥራ ላይ በማሳተፍ ገቢያቸውን ማሳደግ፤
- የተሸሻሉ የእንስሳት ዝርያ ፣ መኖና የእንስሳት ህክምና አገልግሎቶችን እንዲሁም የተሸሻሉ መሳሪያዎችን ለሴቶች በበቂ መጠን መቅረባቸውን ማረጋገጥ፤
- ሴቶች በምርቶቻቸዉ የወጪ ንግድ መርና የገቢ ንግድ ምርቶችን እንዲያካትቱ ማድረግ፤
- የሴቶችን የስራ ጫና እና የጉልበት ብዝበዛ ለመከላከል ጠንካራ የኢንደስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ በመገንባት ሂደት ሴቶች ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ቴክኖሎጂ ተደራሽ እንዲሆን መስራት፤
- የማዕድን ሃብት ልማት ጥናት፣ ፍለጋ፣ ማውጣትና ለገበያ ማቅረብ፤ በተለይ ለሃገር ውስጥ ባለሃብቶች በግል እና ከመንግስት ጋር በጋራ ለማልማት በሚደረገዉ እንቅስቀሴ ዉስጥ ሴቶች ተሳታፊ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ መስራት፣
- የብዙሓን ሴቶችን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችለዉን የአገልግሎት ዘርፉን ማሳደግ፣

- ለሴቶች የኢኮኖሚ እድገት ከሚያመጣዉ ጉልህ አስተዋፆ በመነሳት የኢኮኖሚ ሴክተሮችን ውጤታማነት እና ቅልጥፍና ለማሳደግ በሚደረገዉ እንቅስቃሴ ዉስጥ የአመራርነት ሚናን መወጣት፣

- ሎጂስቲክስንና የመሰረተ ልማትን መሟላት ለሴቶች ከሚያስገኘዉ ጠቀሜታ መመልከት፣

- የኢኮኖሚ ዕድገት ጠቅላላ ሀገራዊ ምርትን ከማሳደግ ባሻገር የህዝቦችን ሰብዓዊ ልማት እንዲሁም የሴቶችን የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥ አገራዊ ፋይዳዉ የጎላ ስለሚሆን ይህንን ያማከለ እና ለማሳካት የሚያስችል እንቅስቃሴ እንዲኖር መስራት ፣

- ለሁሉም ሴት የኢኮኖሚ ተዋንያን ፍትሃዊና ተመጣጣኝ የዕድገት እድል እንዲፈጠር በማድረግ በተፈጠረዉም ዕድል ሴቶች እንዲጠቀሙ ማድረግ፤

- በቀጣይ ሴቶችም ሆኑ ቀጣይ ትውልዱን ኪሳራ ላይ የማይገነባ መሰረተ ፅኑ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስገንዘብ እንዲቻል ለማድረግ የሴት ኢንቨስተሮች ቁጥር እንዲበራከት መስራት፤

- ሀብት ፈጠራን የምታሳድግ ሴት በተለይ ሴት ወጣቶችን በዕውቀት መር ኢኮኖሚ በመገንባት የኢኮኖሚዉ ተዋናይ እንዲሆኑ ማድረግ፤

- የገጠር ልማትና የከተማ ልማትን በማቀናጀትና በማስተሳሰር ለሴቶች የኑሮ መሻሻል እና እድገት ከሚያስገኘዉ ጠቀሜታ በመነሳት መዋቅራዊ ሽግግር ማረጋገጥ የሚያስችል ኢኮኖሚ በመገንባት የከተማ ልማትን ለማስፋፋት የሚደረገውን ጥረት መደገፍና በሂደቱ የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤
- በከተማ ልማትና ኢንድስትሪ ዘርፍ ዋናው ትኩረታችን የዕድገታችን ምንጭ በሆነው በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ላይ አድርገን በሴቶቾ ዘንድ በእድገት ተኮር ዘርፎች በመሰማራት ረገድ የሚታዩ የአመለካከት ማነቆዎችን በመፍታት ሴቶች በስፋት በተደራጀ መንገድ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን፤
- በኢንድስትሪ የሚሰሩ ሴት ላብ አደሮችን በአደረጃጀት ተደራጅተዉ አንድም ለአገራቸዉ ብልፅግና የበኩላንቸዉ አስተዋፅኦ እንድያበረኩቱ በሌላ መልኩም በፆታቸዉ ተደራጅተዉ ትግል እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
- ለሁሉም ሴቶች ፅዱ ምቹና ለኑሮ ተስማሚ  አረንጓዴ ከተሞችን ለማልማት የሚደረገው ጥረት በሴቶች  የተሟላ ተሳትፎ እንዲሳካ በማድረግ የሴቶቻችንን ኑሮ ምቹ ማድረግ፤
- ስራ አጥ የሆኑ አባላትና አባል ያልሆኑ ሴቶችን በማደራጀት የስራ እድል በመፍጠር ወደስራ በማስገባት ገቢአቸውን ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት በመደገፍ የክህሎት

ስልጠና፣ የብድር፣ የግብዓት አቅርቦትና የገበያ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል ስራ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲሰራ የመሪነት ሚና በመጫወት በሂደቱ ሴቶች በተሳትፎ ብቻ ሳይሆን ተግባራትን በላቀ ደረጃ በጥራትና በቁርጠኝነት ለመፈጸም በተደራጀ መንገድ እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ፤

- የሴቶች የቁጠባ ባህል በማዳበር እንዲቆጥቡ በመድረግ የቆጠቡትን ቁጠባ ለላቀ ኢንቨስትመንት እንዲዉል በማድረግ ተጠቀሚነታቸዉን ይበልጥ ለማጠናከር ወደ ህብረት ስራና ወደ ሌሎች የላቀ ጥቅም የሚያስገኙ አሰራሮች ዉስጥ እንዲገቡ ማድረግ፤
- ሴቶች በተሰማሩባቸው ወስኮች ዙሪያ የራሳቸው የህብረት ሥራ ማህበራት እንዲያደራጁና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፤
- የአከባቢ ጥበቃ ስራዎችን በተደራጀ አግባብ አጠናክረን በመቀጠል ለአየር ንብረት ለዉጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚደረግዉ ሁሉ አቀፍ ርብርብ ዉጤታማ እንዲሆንና ሃገራችን የአረንጓዴ ልማት ማእከል እንድትሆን በማድረግ የተፋሰስ ልማትና የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ስራ ላይ አባላት መላ ሴቶችን በማንቀሳቀስ አደረጃጀታቸዉን በመተጠቀም የላቀና የተደራጀ ተሳትፎ ማረጋገጥ፤
- የሴቶችን የሥራ ጫና ለመቀነስና ገቢያቸውንም ለማሳደግ የሚያስችሉ ግኝቶችን ማጠናከርና ማበረታታት፣ የጥናት ግኝቶቹንም አሰባሰቦ ማንኛውም ሰው ሊጠቀምባቸው እንዲችል ማመቻቸት፤

**የማህበራዊ ፕሮግራም ዓላማ፡-** ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጥ አካታች እና የሴቶችን ማኅበራዊ ልማት ያገናዘበ የሚያበረታታ የእድገትና ፍትሐዊ ተሣትፎና ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ፤ ሴቶችን ዝቅ አድርገው የሚመለከቱ አስተሣሰቦችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በማስወገድ፤ የሴቶችን የሥራ ጫና በማቃለል፤ ይህንንም እንደመብት በመመልከት የማኅበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽና አካታች በመሆን በሁሉንም ደረጃ ለሚኖሩ ሴቶች መድረሱን ማረጋገጥ ይሆናል፡፡

**የማኅበራዊ ፕሮግራም ግቦች፡-**

- ፍትሐዊ፣ ጥራት፣ ያለዉ እና አግባብነት ያለው የትምህርት ሥርዓት እንዲኖር በመታገል ሁሉም ሴቶች የትምህርት እድል እንዲያገኙ እና መማር መብትም ግዴታም በመሆኑ ትምህርት ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፤

- የትምህርትና ሥልጠና የማስፋትና ጥራቱን የመጠበቅ ሥራን አጠናክሮ በመቀጠል ሂደት ልማታችንን ለማፋጠንና ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የተላበሰ ብቁ ዜጋ ለማፍራት በሚደረገው ርብርብ በትምህርት ዘርፍ የተቀመጡትን የልማት ግቦች

ለማሳካት መጠነ ማቋረጥ እንዲቀንስ ፣ እድሜያቸው ለትምህርት ደርሶ ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ እና ያልተማሩ ሴቶችም የተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት እንዲማሩ እናቶች ላይ በተደራጀ መንገድ መስራት፤

- መከላከልን መሠረት ያደረገ የጤና ፕሮግራም በብቃት ተተግብሮ የእናቶችን በጤና ተቋም የመገልገል እና የወሊድ ህክምና አገልግሎት ተስፋፍቶ የእናቶችን እና የጨቅላ ሕጻናትን ሞት ለማስቀረት በሚደረገው እንቅስቃሴ ተገቢውን ሚና በመወጣትና ሴቶችን በተገቢው በማሳተፍ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ፤

- በሴቶች ላይ የሚደርሱትን የተለያዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለበርካታ ሴቶች የጤና ቀዉስ ተጋላጭ የሚያደረጋቸውና በሴቶችላይ የሚደርሱትን ፆታዊ ጥቃት ላይ በአደረጃጀት የመታገልና ለተፈፀሙ ጉዳቶች ተመጣጣኝ ፍትህ እንዲያገኙ የተጠናከረ ስራ የመስራት፤
- የሀገራችንን አቅም ያገናዘበ የማኅበራዊ ጥበቃ ሥርዓት እውን እንዲሆን በመታገል የሴቶችን የፖለቲካና ኢኮኖሚ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማጎልበት መቻል፣ በተለይ አካል ጉዳተኞች፣ ተጋላጭ ሴቶችና አቅመ ደካሞች ተጠቀሚ ሆነዉ አቅማቸዉን የሚያጎለብቱበት ሁኔታ ላይ በአደረጃጀቶቻችን አማካይነት ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፤

- አቅመ ደካማዎችንና አረጋዊያን ሴቶች ልዩ ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ መፍጠር እና በአስቸጋሪ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ተጋላጭ ሴቶችን በማህበራዊ በኢኮኖሚያዊና ስነ ልቦና ድጋፍ እንዲያገኙ ዕድል መፍጠር፤

- ብዝኃነታችንን ማዕከል ያደረገ የባህል ቅርስ ልማት ዉስጥ የሴቶቻችን ሚና ጎልቶ ተሳታፊነታቸዉ እና ተጠቃሚነታቸዉ እንዲረጋገጥ እና የሴቶች መልካም እሴቶች እንዲዳብሩ መስራት፤

- በየእርከኑ የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚጎዱ የተለያዩ አስተዳደራዊ በደሎችን ፣ ከመሬት ተጠቃሚነት፣ ከፆታ ጥቃት፣ ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ወዘተ… ጋር ተያይዞ በየአካባቢው የሚታዩ ጉዳዮችን በዝርዝር በመፈተሽ የሚታዩ ማነቆዎችን ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ትግሉን በብቃት መምራት፤

**የውጭ ግንኙነት ዓላማ፡-** እንደ ብልጽግና ሴቶች ሊግ የሚኖረን የውጭ ግኑኝነት ሀገራዊ ክብርን ማዕከል ያደረገ እንዲሆን ማድረግ፡፡

- የውጭ ግንኙነታችን የዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ግንባታን የሚያረጋግጥ፤ የሀገር አንድነትን በማስጠበቅ ሀገራዊ ክብርን የሚያጎናፅፍ፤ ሀገራዊ ክብርን በማጎናጸፍ ሀገራዊ አንድነትን የሚያጠናክር ይሆናል፡፡
- እንደ ሊግ አስቀድሞ የተፈጠሩ ግንኙነቶችን በማጠናከር እና ግድፈቶችና ጉድለቶችን ለይቶ በማስተካከል እና በመሙላት የነበሩ ጠንካራ ጎኖችን ማስቀጠል፤

**የውጭ ግንኙነት ግቦች**

- ሊጉ በየደረጃው ከአሉት ማህበራት ጋር በመተባበር በጋራ ጉዳዮች ዙሪያ የመስራት ሁኔታ እንዳለ ሆኖ ከሌሎች ሀገሮች ሊጎች ጋርም በሀገሪቱ የውጭ ፖሊሲ እና የብልፅግና የውጭ ግንኙነት መርህ ላይ በመመርኮዝ ግንኙነት የማድረግና እህትማማችነትን የማጠናከር፤ የመደጋገፍ፤ ልምድ የመለዋወጥ ተግባራትን ሊያከናውን ይችላል፡፡ በሂደቱም የሚከተሉትን ግቦች እናሳካለን፡-
- በሀገራዊ ክብርን እና ጥቅምን የሚያረጋግጥ የውጭ ግንኙነት ፣
- ለትብብርና ለጋራ ተጠቃሚነት ትኩረት በመስጠት አጋሮቻችንን ማስፋፋት፣
- ለጎረቤት ሀገራት ትኩረት በመስጠት ዘርፈ ብዙ የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣
- የኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ተሳትፎ ማሳደግና በጾታቸው ምክንያት የሚደርሱ ጥቃት በተደራጀ መንገድ መታገል፣